# አሁንም ጉልቻ ቢለዋወጥ
# ወጥ አያጣፍጥም!

## ዶ/ር ኮለኔል ዓቢይ አሕመድ አዲስ ጠቅላይ ሚኒስቴር ሆኖ ስለመመረጡና ከመካከላችን ያሉትን አድርባዮች ስለማጋለጡ


አቶ ሰውየው በሀገሩ
(ዞብሔረ-ኢትዮጵያ ከሰሜን አሜሪካ)


በመጀመሪያ በዚህ ሳምንት በአሜሪካ ኮንግሬስ በከፍተኛ ድምጽ ያለፈው "*H. RES. 128 Supporting respect for human rights and encouraging inclusive governance in Ethiopia*" የተባለውን የሰብአዊ መብት በኢትዮጵያ እንዲከበርና ሁሉን አቀፍ የሆነ ሥርዓት በሀገሪቱ እንዲኖር ጥሪ የሚያደርግ ውሳኔ ሊተላለፍ የቻለው ላለፉት ዓመታት የኢትዮጵያ ሕዝብ በዘረኞች አልገዛም ብሎና ከፍተኛ መስዋዕትነት ለዓመታት ከፍሎ በማመጹ ነው። ይህ ጮቤ የሚረገጥለት ውሳኔም የመጨረሻው አይደለም። ገና በሴኔት ውስጥ ተማሳሳይ ዓይነት ውሳኔ አልፎና ድምፅ ተሰጥቶበት ካለፈና በፕሬዝዳንቱ ተፈርሞ የመንግሥቱ የውጭ ጉዳይና የገንዘብ አስተዳደሩ ክፍል በሥራ እንዲያውል ትዕዛዝ ከፕሬዝዳንቱ ሲተላለፍላቸው ለምሳሌ በውሳኔው ውስጥ የተጠቀመው በወያኔ ባለሥልጣናት ላይ ዕቀባ እንዲደረግ የሚለው በገቢር ሊውል ይችል ይሆናል። ይችል ይሆናል ለምን አልክ ብትሉኝ ውሳኔው በሴኔት ውስጥ ሲያልፍ ልዩ ቅርጽ ሊይዝ የሚችልበት ወይም ከናካቴው ሊከሽፍ የሚችልበት ሁናቴ ሊመጣ ስለሚችል። በትንሹ ወያኔ የመረጠው ጠ/ሚኒስቴር ሁኔታዎችን እያሻሻለ ነው የሚያሰኝ የማደናገሪያ ሥራውን በመሥራትና በዋሺንግተን ሎቢ ማድረጉ ስለማይቀር። በዲያስፖራና በሀበር ቤት ያሉ ተቃዋሚዎችን ዘፈን ለሰማን ደግሞ የወያኔን መሠሪ ወጥመድ ማየት አያስቸግረንም። ስለሆነም የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ከምግዜውም የበለጠ ተፋፍሞ እንዲቀጥል በማድረግ ሚዛኑ ወደ ሕዝቡ ሲያጋድል ምዕራባውያኑም ተገደው እንደነዚህ ያሉ ውሳኔዎችን ጥርሥ ያላቸውና የሚናከሱ አድርገው በሥራ ይተረጉማሉ ማለት ነው። ሙሉውን የዲፕሎማሲ ድል በእጃችን ሳናስገባ በችኮላ ካለጊዜው ጮቤ በመጨፈር እንዳንዋዛ ጥንቃቄ ማድረግ ይኖርብናል ለማለት ነው። ባጭሩ የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግሉን ለአንዲት ደቂቃም ቢኖን ማቀዝቀዝ አይኖርበትም። አቢይ የሞቀውን የኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል እንዲያቀዘቅዝ ወያኔ የጣለው የሽወዳ ካርታ ነው!

በሌላው በኩል ደግሞ ለሁሉም ግልጽ መሆን ያለበት የኢትዮጵያ ሕዝብ በሠላም ሊኖር የሚችለው የወያኔዎች ግፍ የተሞላበት ሥርዓት ከነተለጣፊዎቹና ከነሰንኮፉ ከሥር ተመንግሎ <u>ፍትሕ በተሞላበት ሕዝባዊና ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት ሲተካ ብቻ ነው</u>። ከዚያ ባነሰ በዕርቅ ስም ያለውን ሥርዓት ለጣጥፎ በልዩ መልክ ለማስቀጠል የሚደረገውን በውጪ በምዕራባውያን ዕርቅ የሚሉት ግፊትም ሆነ አገር በቀል አድር ባይ ኃይላት ገና ሳይከካ ተቦካ ዓይነት ጥድፊያ የእንታረቅ ጫጫታ ሊያመጣ የሚችለውን የሕዝብ ትግል ውጤት ቅልበሳ በግምት ውስጥ በማስገባት አገር ወዳድ ኃይሎች በንቃት መጠባበቅ ይኖርባቸዋል። እንደየ ሁናቴዎም ከሕዝቡ ማካከል የሕዝቡን ድምፅ እያሰሙ ከመካከላችን የሚፈሉብንን አውገርጋሪዎች በማጋለጥ ትግሉ ከግቡ እንዲደርስ የቻልነውን ሁሉ ማድረግ ይጠበቅብናል። ወያኔ ለሦሥተኛ ጊዜ በውጪም ሆን በአገር በቀል ጠማሞች እየተረዳ አየነመራ የመጣውን ሕዝባዊ ማዕበል ሊያዳፍነው ቀርቶ ዕድልም ሊሰጠው ከቶውንም አይገባም።

**አሁንም ጉልቻ ቢለወወጥ ወጥ አያጣፍጥም!**

ዶ/ር ኮለኔል ዓቢይ አሕመድ አዲሱ ጠቅላይ ሚኒስቴር ሆኖ ተመረጠ፣ ለኢትዮጵያችን የብሩህ ጊዜ ተስፋን የሚያበስሩንና ከናካቴው የወያኔ የድራማ መልዕክት እያሞካሹ ትልቅ ለውጥ እንደሚመጣ የተስፋ ዳቦአችንን እየገመጥን እንድንጠብቅ በየሚዲያው ሁሉ እየተደሰኮረብን ነው። ከወያኔና ከደጋፊዎቹ የበለጠ የሚያሳዝነው የተቃዋሚ ወገን ነን የሚሉን አድርባዮች የሚከተለውን ዓይነት መግለጫ በድርጅታቸው በራሪ ወረቀት ሲያሰራጩብን መመልከቱ ነው። እነሆ ሸንጎ የሚባለው አሳዛኝ ቡድን ከብዙዎቹ የተቃወሚ ድርጅቶች ነን ከሚሉን ለምሳሌ ያክል ያወጣውን መግለጫ በከፊል ያንብቡ፥ አብዛናዎቹ በዲስፖራ ያሉ ማፈሪያ ስብስቦች ተመሳሳይ አቋምና መግለጫዎች እንዳወጡ አውቃለሁ።

> "ምርጫችን መለያየት ወይም መበታተን ሳይሆን መደመር/አንድ መሆን ብቻ ነው። አማራና ኦሮሞ በወንፊት እንኳ እንደማይለያዩ ሥርገኛ ጤፍ ማለት ናቸው። ታሪካችን የአንድነትና በአንድነት አብሮ የመሥራት ታሪክ ነው፤ ለዚህም የፋሲል ግምብ ግምባታና አድዋ በቂ ምሣሌዎቻችን ናቸው። ይህ አገር የወረስነው ሳይሆን ከልጆቻችን የተዋስነው አገር ነው።" አቢይ አሕመድ (ዶ/ር) ዶክተር አቢይ አህመድ የሚለውን ጥቅስ ያስቀምጥና ይቀጥላል፡-
>
> ከቅርብ ጊዜ ወዲህ፤ ከላይ የተጠቀሰውን መሰል፤ በርካታ ቀስቃሽና አገር ወዳድ ንግግሮችን በማሰማታቸው በኢትዮጵያ የፖለቲካ መድረክ ላይ በአጭር ጊዜ ውስጥ ገዝፈውና ተወዳጅ ሆነው ብቅ ያሉ ኢትዮጵያዊ ናቸው። በአገር አቀፍ ደረጃ ስማቸው አሁን ጎልቶ ተሰማ እንጂ፤ እነ አቶ ለማ መገርሳና አዲሱ አህዴድ ለጀመሩት ለውጥ እንደ አንድ ዋነኛ አጋር ሆነው፤ ድምጻቸውን አጥፍተው ሲሰሩ እንደቆዩ ይነገራል።
> ሸንጎ በአንድ በኩል እንዲህ ዓይነት ችሎታና አገር ወዳድነት በአያሌው የተለገሳቸው ግለሰብ ለአገር መሪነት መመረጣቸውስ የሚል ዜና መሆኑን እየገለጽን፤............"

ለነገሩ ሸንጎ ለሚባለው "ሕብረት" ከመነሻው ከበሬታና ዕውቅና ያልሰጠሁት ቡድን ስለሆነ ብዙም ባይደንቀኝም ዓብይ አሕመድ ኢትዮጵያ ላለችበት የፖለቲካ አጣብቂኝ መፍትሄ ሊሆን ይችላል ብለው ሊያሳምኑን ከሸንጎ ሌላ ሌሎች ለሕዝብ እየታገልን ነው ሲሉን የነበሩ ሁሉ የሚሯሯጡ ብዙ በርክተዋል። እንዲያውም ወያኔ ሥልጣኑን ለሕዝብ ለቀቀ ሊሉን አንድ ሐሙስ የቀራቸው ይመስላሉ። የሚያስገርመው በአንድ በኩል ኢትዮጵያዊነትን የሚጠሉት እነ ጃዋር መሐመድ፣ሊንጮ ለታ፣ ዲማ፣ የመሳሰሉት በሌላ በኩል የወያኔ ደጋፊዎችና የሕዝቡን ትግል ገዳዮች እንደነ ልደቱ ዓይነቱና ወያኔን እንቃወማለን የሚሉን እንደ ሸንጎ፣ ግንቦት ሰባት ዓይነቶቹ ኮከባቸው ገጥሞ ወያኔ ለሦሥተኛ ጊዜ ራሱን ከሕዝብ ዓመጽ ለማዳን ባዘጋጀው ወጥመድ ለመግባት ሲሽቀዳደሙና የሕዝቡን ትግል ዳግመኛ ሊያስመቱ ሲንቀሳቀሱ ለተመለከትን ያስገርማል። ይሄን ሁሉ ቅሌት ለታዘብን ደግሞ መንገዱን ጭርቅ ያድርግላችሁ ከማለት ሌላ መልዕት የለንም።በኔ በኩልማ አዚህ ዲያስፖራ በኢትዮጵያዊነት ተጠናክረን እንዳንሰባሰብ ታጋዮች መስለው የሚያለያዩን ተቃዋሚ ድርጅቶች ነን የሚሉን ከኢሕአፓ በስተቀር ሁሉም ለጠቅላይ ሚነስትሩ ጊዜ ይሰጠው እያሉን ነው። ግማሾቹም ከተጠሩ ገብተው ለማገልገል ዝግጁ መሆናቸውንም እያሰሙን ነው። በበኩሌ ለመሳፈሪያቸው ዕርዳት ቢጠይቁኝ በደስታ እረዳለሁ። በዲያስፖራ ያለው ሕብረተሰብም በመካከሉ መተማመን እንዳይኖር ያደረጉና ሀገር ወዳድ ድርጅቶች ተሰሚነት እንዳይኖራቸው ብዙ ጫጫታ ያደርጉ የነበሩ መፈሪያዎች ሁሉ ተጠራርገው ከፊታችን ስለሚሄዱ ባቁላ አለቀ ፈስ ቀለለ ነው።

ጠቅላይ ሚኒስትሩ ሰሞኑን አገር ውስጥ እየተዘዋወረ ንግግርና ቅስቀሳ ሲያደርግ በትግራይ መቀሌም ሄዶ የወያኔዎችን ጫማ መላሱ እውነተኛ መልኩንም አሳይቶናል። ለተግቸለቸሉት ተቃዋሚዎች በሉን ጉዶች ይብላኝ እንጂ ጠቅላይ ሚኒስትሩ የትግራይን ሕዝብ ወርቅ ሕዝብ ብሎ እንደ መለስ ዜናዊ በትግሪኛ ሲናገር በሌሎች ከተሞች ንግግር ሲያደርግ ግን የወርቅ ሕዝብ ሲል አልተሰማም። <u>ግፈኛ</u>

ስርዓቶች ተፈራረቁበት እንጂ መላው የኢትዮጵያ ሕዝብ ወርቅ ሕዝብ ነው! ለመብቱና ነፃነቱ ሁሉም ኢትዮጵያዊ ከፍተኛ መሥዋዕትነት ከፍሏል። ወያኔ የጀግኖች ስብስብ ሳይሆን ኢትዮጵያን የካዱ የባንዶች ስብስብ ነው። ታዲያ መቀሌ ሄዶ ወያኔን ማዳነቅ ምን የሚሉት ነው? የዚያ ትውልድ መስዋዕትነትን አያውቀውም ይሆን? ወይስ ወያኔ ያሳደገው ስለሆነ ይሆን? ውሻ በበላበት ይጮኻል ይባል የለ? ወያኔ ኢትዮጵያዬ! ኢትዮጵያዬ! ቢል ቢዘምር እየተነሳሳ ያለው የኢትዮጵያ ሕዝብ የአምጽ ማዕበል ከፊቱ ተደግኖ ስላየው የሕዝቡን ድምጽ ይዞ ሊሮጥ ያዘጋጀልን በመርዝ የተወጠወጠ ድግሥ ነው። እኛም ነቅተናል ነው መልሳችን መሆን ያለበት።

ብዙ ሀገር ወዳዶችንም በወያኔ የትግል መግደያ ወጥመድ ለማስገባትና ከዕለት ወደ ዕለት እየጋለና ኢትዮጵያዊነትን አድምቆ ትልቅና የማይበገር ኃይል እየሆነ የመጣውን ሕዝባዊ ዓመጽ ለማቀዝቀዝ ወይም ለማምከን ወያኔና መሰሎቹ አይሸርቡት ተንኮል፣ አይገለብጡት ድንጋይ እንደሌለ መዘንጋት የለበትም። አቅጣጫ በማሳት ለመምታት አደገኛ ዝግጅት እየተደረገ እንደሆነ ሁላችንም ነቅተን ልንጠብቀው የሚገባን ጊዜ ነው። አህያ ልጇን ሊበላ የመጣውን ጅብ ማስጣል ቀርቶ ራሷንስ መከላከልስ ትችላለች? እንግዲህ አዲሱን ጠቅላይ ሚኒስቴር አስመልክቶ መልሴ አሁንም ጉልቻ ቢለዋወጥ ወጥ አያጣፍጥም ነው።

አዲሱ ጠ/ሚኒስቴር  ሀገሪቱ ለምትፈልገው የዴሞክራሲያዊ ለውጥ የሚበጅ ነው ብለው ሊያሻሽጡልን የተነሱብን፣ ማለትም የኛኑ ጠማሞችም ሆኑ የሚነዷቸው የምዕራባውያን መንግሥታትን ጨምሮ በአንደኛ ቁጥር የሚያስቀምጡልን መከራከሪያ ነጥብ ዘሩ ኦሮሞ ስለሆነ በኦሮሞ ሕዝብ ሊታቀፍ ይችላል ይሉና፣ የእስላም ተከታይም ነው ሲሉንም ይደመጣሉ።  የኢትዮጵያ ሕዝብ አመጻ መሠረቱ የጎሳ ክልልን አፈራርሶ ለመጣል መሆኑ ተረሳ እንዴ? መጀመሪያ የጎሳ መታወቂያ ወረቀቱን ያቃጥልና ተአማኒነቱን ለኢትዮጵ ሕዝብ ያስመስክር። ከቀበሌ መታወቂያ ወረቀት አንስቶ፣ የፓስፖርት የመሳሰሉት የሚሞሉ ፎርሞች ላይ ሁሉ የዘር ጥያቄ ለምን አስፈለገ? አንድ ሰው ለመታወቂያው ስም ከነአባትና የሚኖርበት አድራሻ አይበቃም ኖሯል? በኢትዮጵያዊነት ዜግነት የሚያምን ሁሉ የዘር መታወቂያውን ማቃጠል ይጠበቅበታል። በነገራችን ላይ አሁንም እሥሩና ግድያው እንደቀጠለ ነው። ለግድያ ደግሞ ማንም ጊዜ ይሰጠው ሊለን አይችልም አሜሪካኖቹንም ጨምሮ። የአሜሪካ ኮንግሬስ በቅርቡ አሳለፈ የተባለው ውሳኔ በአጭር ጊዜ ውስጥ በትግባር የሚውል ስላልሆነ (በተለይ በወያኔ ባለሥልጣናት ላይ የተጣለው ዕቀባ) ደስ ብሎናል ደስ ይበላችሁ ድግሥ ራስን ማታለል ብቻ ሳይሆን የሕዝቡን መስዋዕትነት መርሳትም ነው! ለዚሕም የተደረሰው እኮ በኢትዮጵያ ሕዝብ አመጽ ነው። ሕዝቡ ደግሞ የወያኔንና የተለጣፊዎቹን ክልል አፍርሶ አብሮነትን መርጧል!  ከኢትዮጵያ ሕዝብ ትግል ለመሰለፍ ኢትዮጵያዊነትን ማቀፍ፣ የጎሣ ባንዲራን ማውለብለብ ሳይሆን የኢትዮጵያን ባንዲራ - አረንጓዴ ቢጫ ቀይ ብቻ ይዞ በመውጣት ለዓለም አንድነታችንን በትግባር ማሳየት ይጠበቅብናል። ከዚያ ያነሰ የአዞ እንባ መርጨት ያክል ነውና እየተስተዋለ።

ኢትዮጵያዊነት በትግላችን ያቸንፋል!
አቶ ሰውየው በሀገሩ ዘብሄረ-ኢትዮጵያ (ከሰሜን አሜሪካ)

1. ስለ ዶ/ር ኮሎኔል ዓቢይ አሕመድ ምስክርነት - አቶ አያሌው መንገሻ የቀድሞ የወያኔ ደሕንነት ሰው ያድምጡ
2. የግንቦት ሰባቱ ነአምን ዘለቀ በቢቢሲ ያለውን ለማድመጥ